# “ጊዜ ዱሮ ቀረ!”

ሰው ተስፋው ሲቀጭጭ- ነገ ሲያስጨንቀው

ዛሬ መከራውን- ግፋን ሲያስቆጥረው

“ጊዜ ትናንት ቀረ! ጊዜ ዱሮ ቀረ! “ - ይሆናል ምስጋናው።

ጊዜ ተስፋ ዳምኖ- የሚዘንብ ሲመስል

ሰው ዛሬ እየከፋው- ይታያል ፈገግ ሲል።

ታድያ ማነው እርሱ- ተስፋን የሚዘራ

በዛሬ የሚተኩስ- የሰው ባላጋራ

ምድር ነው ወይስ ሰው- የተስፋ ጠላቱ

ሰው ነው ወይ እርጉሙ- ወይንስ ምድሪቱ?

እምቅ ሐብት ስይኖራት- ጃፓን ስትበልጥግ

ቻይና እልፍ ህዝቦቿን- አልብሳና አጉርሳ- በፍጥነት ስታድግ

አሜሪካ ሃያል ስትሆን- በአራት ዘመን

የሀበሻ ምድር በችግር ሲታመስ- ሲተላለቅ ወገን

ሃገርም ቢኖረው -መንግስትም ቢኖረው- ሶስት ሺ ዘመን

ማሞገስ መኮነን- ሰውን ወይስ ጊዜን-ወይንስ ምድሪቱን?

ሃበሻ አገር ኖሮት- በታሪክ ላይ ሲጣፍ

አውሮጳ ያን ጊዜ- አልወረደም ከዛፍ

ካሌብ ምድረ-አረብን- አፍሪካን ሲያስገብር

የአማሪካ ምድር- አልተቀኘም ነበር

ጉድም እንድ ጅራት -ከኋላ ነውና

ሀበሻ ሲዋረድ- እያየን ነው ገና።

እናም “ዱሮ ቀረ!” የሚባለው ጊዜ

ነውረኛ ንግግር- ሲገፋም አባዜ

አካፋን አካፉ- የምንል ከሆነ

ሰው ነው እንጅ ከፉ- ጊዜ ምን በደለ?

ትናንት ከሚባለው ትናንት ጀምሮ

ምነው አላቆመም- የሃበሻ ሮሮ

ሲያሳድደው ያለው- ከቦረና አስመራ

ከሃርጌሳ አንስቶ- ሴቲቱ-ሁመራ

ለህዝቡ ጦርነት- ሆኖበታል ስራ።

ጊዜም እንደወትት- ሲገፋ ሲገፋ

ከትናንት የሚሻል-ዛሬ እሚባል ጠፋ።

ሰው ተስፋው ሲቀጭጭ- ነገ ሲያስጨንቀው

ዛሬ መከራውን- ግፉን ሲያስቆጥረው

“ጊዜ ትናንት ቀረ! ጊዜ ዱሮ ቀረ! “ - ይሆናል ምስጋናው።

ዳግማዊ ዳዊት
መስከረም 2003
Ethio_dagmawi@yahoo.com